Title: Mario Bushi, Lansemo Lulo, Tura Harticha, and Elias Gudisa Interview

Creators: Bushi, Mario; Lulo, Lansemo; Harticha, Tura; Gudisa, Elias; Bekele, Getnet

Date: July 30, 2010

City: Ali Wayao

Country: Ethiopia

African Oral Narratives: aodl.org/oralnarratives

እኔ ፕሮፌሰር ጌትነት በቀለ እባላለሁ

ስማችሁን አስተዋወቃችሁኝ ወደ ጥያቄና መልስ እንገባለን፡፡

1. ዋሪዎ በሼ
2. ላንሶሞ አሎሎ ዕድሜ 45
3. ቱራ አርሲቻ ዕድሜ 75
4. ወረዳ አታቻ ዕድሜ 38
5. ኤልያስ ወድሳ ዕድሜ 50
6. ኑራ ለቡ

የምናደርገው ከድሮ ጀምረን ወደ አሁኑ እንመጣለን የምታውቁትን ትነግሩኛላችሁ ስለድሮውም ስለአሁኑም

ጥ. ከአፄ ምኒልክ ዘመን በፊት እዚህ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች የአመጋገብ ሥርዓታቸው እንዴት ነበር ምን ይበላሉ ? ምንስ ይጠጣሉ ? ይህን የሚያውቅ ካለ

መ. ሚር ውተት፣ ገንፎ ይማቡ ነበር በዛን ወቅት ብዙም እርሻ የለም

ጥ. የምን ? ገንፎ ነበር የሚባሉት

መ. የበቆሎና የገብስ ነው በወፍጮም አይፈጭ በዛን ወቅት በእጅ ነበር የሚፈጨው

ጥ. ካላረሱ ገብስና በቆሎ ከየት ይመጣል ?

መ. በቆሎና ገብስ በትንሹም ቢሆን ያመርቱ ነበር

ጥ. በዛን ወቅት አስተዳዳሪያችሁ ማን ነበር ?

መ. አፄ ኃ/ስላሴ ናቸው

ጥ. ከዛ በፊትስ

መ. አናውቅም

ጥ. ቱኬ ማማን የሚያውቅ አለ ወይ ? እስኪ ስለሱ ንገሩኝ

መ. ቱኬ ማማ አስተዳዳሪ ነበር

ጥ. ማን ሾማቸው ?

መ. አፄ ምኒልክ ናቸው

ጥ. ከቱኬ ማማ በፊትስ ማን ያስተዳድር ነበር ?

መ. አፄ ምኒልክ፣ እያሱ፣ ዘውዲቱ

ጥ. እዚህ አካባቢ እርሻ በጣም የተስፋፋው መቼ ነው ?

መ. ከጣሊያን በኋላ በኃ/ስላሴ ጊዜ ነው

ጥ. ምን እህል ነበር በብዛት የሚዘራው ?

መ. በቆሎ፣ ባቄላ፣ ገብስ

ጥ. ስንደስ ?

መ. ስንዴ በቅርብ ነው የተጀመረው

ጥ. በደርግ ነው ስንዴ የመጣው ?

መ. በአፄ ኃ/ስላሴ ሜጨሻ አካባቢ

ጥ. ሌላስ ምን ምን እህል አለ ?

መ. ዘንጋዳ፣ ጤፍ አለ ግን በብዛት አንዘራውም

ጥ. ቀደም ባለው ጊዜ እዚህ አካባቢ ከእርሻ ይልቅ ከብት ነው የሚኖረቡት ይባላል ትክክል ነው?

መ. አዎ ከብት ነው የሚኖረቡት እርሻ በትንሹ ነው ግን ትንሽ ታርሶም በጣም በቂ ነው ከብቶቹ ሳር በደንብ ስለሚያገኙ ወተት ይሰጣሉ ወተትና ቅቤ አለ

ጥ. ከብት መቀነስ የጀመረው መቼ ነው ?

መ. በመንግስቱ ኃይለማርያም ዘመን ነው

ጥ. ለምን ይመስላችኋል ?

መ. ከአፄ ኃ/ስላሴ ሜጨሻ ጀምሮ በመንግስቱ ጊዜ ሰው በዛ ሜዳቱ አለቃ የግጦሽ ሜዳት ጠፋ፣ የቱኬ ማማ ጫቃ ሾሞች ነበሩ በባላባትነት በዛን ወቅት ይዘው እያሉ ነው ደርግ ገብቶ ሜዳት ለህዝቡ የተከፋፈለው ሰው በዛ እርሻም በዛ አየሩም አነሰ በጋና ክረምቱ ተቀላቀለ

ጥ. ህዝብ በዛ እያላችሁ ነው ለምንድነው ነው? ህዝብ የበዛው ሰው ብዙ እየወለደ ነው? ወይስ ከሌላ ቦታ እየመጣ

መ. በደርግ ጊዜ ሰው በብዛት ከተለያየ አካባቢ በምን ምክንያት እንደሆነ ባይታወቅም መጣ እነርሱም ይዋለዳሉ በዚህ ምክንያት ነው

ጥ. በደርግና በአፄ ሀ/ስላሴ ጊዜ ያለው የገበሬው ችግር ምንድነው ? በማጻፀር ቢያቀርቡልኝ

መ. በደርግ ጊዜ ሜዳት ላራሹ በማለት ሜዳቱ ሁሉ ተከፋፍሎ ታረሰ ለሜዳቱ ምንም አልታሰበም በአፄ ሀ/ስላሴ ጊዜ ርስት የባላባት ነበር በነገሌ ወረዳ በቱኬ ማማ ስር 7 ባላባቶች ነበሩ የሜዳት ቁጠባም አልነበር በዛን ወቅት ቤተ ርስት በማለት እስከ 40 ጋሻ ያረሰ አለ፡፡

ጥ. በማግስቱ ጊዜ ዋናው ችግር ምንድነበር የገበሬው ?

መ. ማግስቱ ቃ/ሚርያም ሲመጣ ሜሬት ላራሹ ሆነ ሁሉም ሜሬት አገኘ ምንም ችግር የለም

ጥ. እስኪ እርስዎ በግሎ ሜሬት እንዴት እንዳገኙ በእርስዎ ሜሬት ላይ በራስዎና በቤተሰብዎ ያገጠምዎት ችግር ካለ ቢገልፁልኝ ?

መ. የኛ ችግር በሁለቱ ማግስታት በአፄ ሀ/ስላሴ የምናርሰው ሜሬት በባላባቱ ቁጥጥር ስር ሆኖ እኛ ጭሰኛ ሆነን አንሠራ ነበር ሜሬት በኮንትራት እናገኝና ግብር እንከፍል ነበር፡፡ በማግስቱ ጊዜ ሜሬት ለአራሹ ሆነ በባላባት እጅ የነበረ ሜሬት ከፋፍለው ሰጡን

ጥ. ስንት ጥማድ ሜሬት ነው ያገኙት

መ. አንድ ሄክታር ነው የተሰጠኝ አሁንም እዛው ላይ ነው ያለሁት?

ጥ. አሁን እርስዎ ያሉበት ሜሬት የባላበት ነበር ከሆነ ማን ነበር ባላባቱ?

መ. የባላባት ነበር ፊጋ ቤቶ ይባሉ ነበር

ጥ. እርስዎ ለፊጋ ምን ነበር የሚገብሩት ?

መ. እኔ ለፊጋ ምንም አልገበርኩኝም ትንሽ ነበርኩ ለኔ ሜሬት የተሰጠኝም ደርግ ነው

ጥ. የደርግንና የኢህአዲግን ጊዜ ይወስዱና በእርስዎ ህይወት ላይ ምንድነው በኑሮዎ በእርሻዎ ያመጣው ለወጥ የትኛው ነው?

መ. በሁለቱም ወቅት ያጋጠመኝ ችግር የለም ደርግ ሜሬት ለሌለው ሁሉ እንዲደለደል /እንዲያገኝ አደረገ፤ በኢህአዲግ ደግሞ የያዛችሁትን እንደያዛችሁ ተቀማጡ ተባለ ትንሽም ትልቅም ያለው የያዘውን ይዞ ተቀማጠ አሁን ያለው ችግር ከስር ያሉ ልጆች ሲደርሱ ምን ይሆናሉ የሚል ስጋት አለን ሜሬቱ ስለሌለ፡፡

ጥ. እርስዎ እርሻ ለስንት ዓመታት አረሱ ?

መ. ከ20 ዓመት በላይ

ጥ. በደርግ ጊዜ ግብርና ጀምረዋል ?

መ. አዎ

ጥ. የሜሬትዎ ስፋት ስንት ነው?

መ. አንደ ሄክታር

ጥ. ሜሬትዎ ላይ ምንድነው የሚዘሩት ?

መ. በቆሎ፣ ስንዴና ጤፍ ነው

ጥ. ከብት አለዎት? ካለዎት ስንት?

መ. አዎ ሶስት አለኝ አንድ ላምና አንድ ጥማድ በሬ

ጥ. ሜሬቱን እንዴት አገኙት? ከቤተሰብ በወርስ ነው ? ወይንስ በደርግ ጊዜ ሲከፋፈል ነው ያገኙት

መ. በደርግ ጊዜ ሲከፋፈል ነው ያገኘሁት

ጥ. አሁን እርስዎ በእርሻዎ ላይ ያለው ከፍተኛ ችግር ምንድን ነው?

መ. የዝናብ እጥረት ነው ያለብን ችግር

ጥ. የዝናብ እጥረቱ ምርቱን አሳንሶታል እስኪ በፊት ከሚያመርቱት ጋር አነፃፅረው ቢነግሩኝ ምን ያህል ስንዴ? ምን ያህል በቆሎ

መ. በፊት በሄክታር ሲዘራ 30 ና 40 በቆሎ ይገኛል ስንዴ በአንድ ጥማድ ሰባትና ስምንት ኩንታል አሁን ግን አራትና አምስት ነው የሚገኘው

ጥ. ማዳበሪያ ተጠቅመው ያወቃሉ?

መ. አዎ ያለማዳበሪያ አይዘራም

ጥ. አሁን ማዳበሪያ ተጠቅመው በአንድ ጥማድ ስንት ኩንታል ስንዴ ነው የሚያገኙት?

መ. አራት ኩንታል

ጥ.	በፊት በአንድ ጥማድ ከዚህ የተሻለ ያገኙ ነበር?

መ.	አዎ ሰባትና ስምንት ኩንታል ይገኝ ነበር

ጥ.	ይሄ ችግር በምን ተከሰተ ብለው ያስባሉ?

መ.	የዝናቡ እጥረት ነው

ጥ.	ዝናብ ቢኖር እንደ ድሮው ይሚታል ብለው ያስባሉ የሜሬቱ ለምነት አልተቀየረም?

መ.	አዎ አልተቀየረም ሜሬቱ ለም ነው

ጥ.	እርስዎ እንደዚህ አካባቢ ነዋሪነቶ የአየር ሁኔታው የተቀየረ ይመስልዎታል ለምሳሌ ሙቀት ጨምሯል ወይስ ብርድ ዝናብ በወቅቱ አይመጣም?

መ.	አዎ ከኛ በላይ ያለው አካባቢ ደጋ ይሄ ወይና ደጋ ነበር አሁን ግን የኛ ቆላ ሆኗል፡፡

ጥ.	ዝናብ መቼ ነበር እዚህ አካባቢ የሚጀምረው?

መ.	ሚያዝያ ሲገባ አልፎ አልፎ ማቢት ሜጨሻ ጀምሮ ሚያዝያ ይዘንባል በቆሎ ከሚያዝያ እስከ ግንቦት ይዘራል በመቀጠል ስንዴ ይዘራል

ጥ.	ስንዴና ጤፍ መቼ ነው የሚዘራው?

መ.	ስንዴ ከሰኔ እስከ ሀምሌ ጤፍ ሀምሌ

ጥ.	በቆሎ መቼ ይታጨዳል?

መ.	ህዳር ነው

ጥ.	እስከዛ ይቆያል?

መ.	አዎ

ጥ.	ስንዴና ጤፍስ

መ.	በጥቅምት

ጥ. ከህዳር እስከ ሚያዝያ ገበሬው ምን ይሰራል?

መ. ያጨደውን ይወቃል እንጂ ምንም ሥራ የለውም በጋ ስለሆነ

ጥ. አሁን የክረምትና የበጋ ዘመን የተቀያየረ ይመስልዎታል?

መ. በዝናብ ስናይ ተቀይሯል

ጥ. በዚህን ወቅት ብዙ ማዝነብ ነበረበት?

መ. አዎ አሁን ግን የለም

ጥ. የዝናቡ እጥረት በአሁኑ ዓመት ብቻ ነው የተፈጠረው?

መ. ሶስት ዓመት ሆኖታል

ጥ. የዝናቡ መጥፋት በምን ምክንያት የተፈጠረ ይመስላችኋል ከግብርና ባለሙያዎችስ ጋር ተነጋግራችኋል?

መ. ደን አልቆ ነው ይባላል፡፡ ዝናቡ የሚመጣው ግን ከእግዚአብሔር ነው እሱ እስኪመልሰው ማጠበቅ ነው

ጥ. እርስዎስ ስንት አመት አርሰዋል? ገበሬ ከሆኑ ስንት ዓመቶት ነው?

መ. የህፃንነቴ ከተቆጠረ ረጅም ነው የራሴን ሚስ የጀመርኩት ግን ደርግ ገብቶ በ3ኛው ዓመት ነው

ጥ. መሬት እንዴት አገኙ?

መ. ቀበሌ ነው የሰጠኝ

ጥ. አባትዎ ከዛ በፊት አልነበራቸውም?

መ. አባቴ አላቸው እሳቸው ግን እዚህ ወረዳ አይደሉም ከንባታና ሀዲያ አወራጃ ነው ያሉት

ጥ. ደርግ መሬት ላራሹ ብሎ ሲያከፋፍል ነው ያገኙት?

መ. አዎ ደርግ ገብቶ በ4ኛው ዓመት ነው ያገኘሁት

ጥ.	ምን ያህል ሜት አገኙ?

መ.	ሁለት ተከል ጥማድ ነበር

ጥ.	አሁን ተቀንሷል ወይስ ተጨምሯል?

መ.	ተጨምሮልኛል

ጥ.	መቼ ነው የተጨመረልዎት?

መ.	በ1978

ጥ.	በዛው በደርግ ዘመን ነው የተጨመረልዎ ምን ያህል ጥማድ ተጨመረልዎት?

መ.	ሁለት ተከል ተጨምሮልኝ በጠቅላላው አምስት ሆነልኝ

ጥ.	ማሳዎት ላይ የሚያርሱት ዋና ምርትዎ ምንድን ነው?

መ.	እዚህ አካባቢ ዋና ምርታችን በቆሎ ነው በመቀጠል ስንዴ ሌላ ለማምረት ሰፊ ቦታ ስለሌለን በማጡ ነው፡፡

ጥ.	እርስዎ እርሻ ለምንድነው የሚያርሱት?

መ.	ለመኖር ለራሴና ለቤተሰቤ ብዬ

ጥ.	ለገበያ ብለው አስበው ያውቃሉ እርሻ ሲወጡ

መ.	እራሴንና ቤተሰቤን ከቀለብኩ በኋላ ቤቴን እኔ የምፈልገውንም ለመግዛት /ለልወውጥ/ ነው የምሸጠው

ጥ.	ወደ እርሻ ሲወጡ ግን የሚያስቡት እራስዎንና ቤተሰብዎን ለማስተዳደር ነው?

መ.	አዎ

ጥ.	እቤታችሁ ወስጥ ብዙ ጊዜ የምትመገቡት ምግብ ከበቆሎ የተሠሩ ምግቦችን ነው?

መ.	አዎ በአንደኝነት የምንመገው ከአረስነው በቆሎ ነው

ጥ. ከአረሳችሁት ምን ያህል ተርፏችሁ ትሸጣላችሁ በዓመት?

መ. በአሁኑ ወቅት ብዙም ትርፍ የለም ያው ለልወጭ ያክል ነው የምንሸጠው

ጥ. መጀመሪያ ማዳበሪያ መቼ እንደተጠቀሙ ያስታውሳሉ?

መ. በ1974 ነው

ጥ. የማዳበሪያን ጥቅም ማን አሳየዎት?

መ. የማዳበሪያ ጥቅምን መጀመሪያ ያስተማረን የግብርና ባለሙያ ነው

ጥ. መቼ?

መ. በ1974

ጥ. በደንብ ስለአጠቃቀሙ ተምረዋል ማዳበሪያውስ ጠቅምዎታል?

መ. አዎ ያኔ ጠቅሞኛል

ጥ. እንዴት ?

መ. በፊት ገበሬ ሙሉ በሙሉ ያለማዳበሪያ ነበር የሚጠቀመው ቀስ በቀስ የግብርና ባለሙያ እያስተማረ ህዝቡም ይጠቀም ጀመር ገበሬውም ተማረ ዕውቀትም ሲመጣ ይጠቀም ጀመር፡፡

ጥ. የማዳበሪያ ጥቅም ምንድነው ተብለው ቢጠየቁ ምን ይላሉ?

መ. የማዳበሪያ ጥቅም ምርቱ ከፍ ይላል በባዶ ከሚዘራው የተሻለ ነው

ጥ. ማዳበሪያ ጉዳት ያስከትላልስ ብለው ያስባሉ?

መ. አዎ ጉዳት አለው ጉዳቱም በፊት 35 እና 50 ብር ነበር ገዝተን የምንጠቀመው አሁን 450 ብር ገብቷል አንድ ኩንታል ስንደና 50 ኪሎ ማዳበሪያ እኩል ነው በገበያ ላይ እኔ 2 ሄክታር አርሳለሁ ብል የምጠቀመው 200 ወይም 300 ኪሎ ማዳበሪያ ያስፈልጋል ስለዚህ 5 ኬሻ ስንዴ ብሸጥ የምጠቀመውና የማገኘው የተለያየ ነው ገለባና የተወሰነ ትርፍ ከተገኘ ነው እንጂ እርስ

በርስ መቀየር ነው፡፡ ድሮ ግን 40 ና 50 በምንገዛበት ጊዜ አንድ ጥማድ ስንዴ ከ5-6 ኩንታል ይገኝ ነበር ስለዚህ አሁን ብዙ ዋጋ ተከፍሎ ነው ምርት የሚገኘው

ጥ. ይህንን ችግር በምን ምክንያት የመጣ ይመስላችኋል?

መ. በመጀመሪያ ደረጃ አየሩ ተለውጧል፡፡ እዚህ አካባቢ በፊት አንድ ቀን ዝናብ ከዘነበ እስከ 4 እና 5 ቀን ጭቃ ነበር የሚሆነው አሁን መሬቱ አሸዋ ሆኗል፡፡ ጭቃ የለም፡ ዝናቡም በወቅቱ አይመጣም ደረቅ አየር ነው ያለው ዝናብ ከመጋቢት ጀምሮ ይዘንባል በሚያዝያ አርሰን እንጨርስ ነበር አሁን ግን ይሄ የለም፡፡

ጥ. ዝናብ ቢኖር ሌላው ነገር ባይኖርም ጥሩ ምርት ይገኛል ብለው ያምናሉ?

መ. አዎ አምናለሁ ገበሬው አሁን ተምሯል ዝናብ ቢኖር ጥሩ ያርስ ነበር

ጥ. መሬት መቼ እንዳገኙ ቢነግሩኝ?

መ. እኔ መሬት ያገኘሁት መንግስት ሰጥቶኝ አይደለም ከአባቴ በወርስ ነው ያገኘሁት አባቴ በፊት ሲቀበል በባለርስት ስር ይተዳደር ነበር መሬት በደርግ ቁጥጥር ስር ሲሆን የባለርስቱን መሬት አባቴ ወረሰ፡፡ እኔ ደግሞ ከአባቴ ወረስኩ፡፡

አንድ መንግስት ሄዶ ሌላ ሲመጣ ለወጥ አለ በአፄ ኃ/ስላሴ ዘመን መሬት ነበር ግን አይታረስም በትክክል ሚዜስ የጀመርኩት በኢህአዲግ ዘመን ነው 5 ጥማድ መሬት አለኝ ገብስ በቆሎ ስንዴ እዘራለሁ ሌላውን እንዳልዘራ የመሬት ስፋት ያንሰኛል

ጥ. በአንደኛ ደረጃ ስንዴ ከዛ በቆሎ ነው የሚያርሱት?

መ. ከሚያዝያ እስከ ሰኔ በቆሎ እያልን በየተራና በየወቅቱ ስንዴ እያልን በመቀጠል እንዘራለን ማዳበሪያ በደርግ ጊዜ ደርግ ድጎማ እየከፈለ ይሰጠን ነበር ገበሬም በዚህ ይጠቀም ነበር አሁን ግን በነጋዴ እጅ ስለገባ ማዳበሪያው በጣም ተወደደ መሬቱ ማዳበሪያ ስለለመደ በኮምፖስም ማጠቀም አልቻልንም ስለዚህ በጣም ችግር አለ የምግብ እጥረት ሁሉ አንድ ሰው የሚሰራው ለመብላት፣ ለመኖር ለመማር በማሆኑ ብዙ ወጪዎች አሉ የሰው ብዛትና የመሬት እጥረት አለ፡፡ የገበያውንም ሁኔታ ስናይ ማዳበሪያ በቆሎና ስንዴ ዋጋው አንድ ሆኑ ከዚህ በተጨማሪ የአየር ማዛባት

ያስከተለው ችግር ነው ይህም ከሆነ ከ3 ዓመት በላይ ሆኗል፡፡ በዚህ ምክንያት አንድ ሜት ሰባት እና ስምንት ኩንታል የሚወጣው በአየሩ ማዛባት ሶስት እና አራት ኩንታል ብቻ ይሚታል፡፡

ጥ. ድጎማን በተመለከተ ከፍተኛ ባለስልጣኖችን አነጋግረን ነበር እነሱ የሚሉት ገበሬዎች የእህል ዋጋ ስለጨመረ ያለ ድጎማ ማዳበሪያ መግዛት ይችላሉ? የላሉ ይህን እንዴት ታዩታላችሁ?

መ. ያንን መወሰን የምንችለው ዋጋው ከፍ ዝቅ ሲል ነው የምንኖረው በአቅም ስለሆነ ይሄ ትክክል አይደለም እኛ አቅም ስለሌለን መንግስት ድጎማ አድርጎ ቢያቀርብ ጥሩ ነው፡፡

ጥ. ከመንግስት ሃላፊዎች ጋር ስንነጋገር የሜት የባለቤትነት ጉዳይ አለ ሜት ግን የማን ነው? መሸጥ መለወጥስ ትችላላችሁ

መ. ሜት በፊት በግለሰብ እጅ ወይም በባለርስት እጅ ነበረች አሁን ግን ሜት የመንግስት ነው ተብሏል ኘላኑ ወጥቶለት ግን ለእያንዳንዳችን ተሰጥቶናል፡፡ መሸጥ መለወጥ ግን አንችልም

ጥ. እርስዎ አሁን ሜትዎን በሽጡ በለወጡ ደስ ይሉዎታል?

መ. እኔ መሸጥን አልወድም አልፈልግምም

ጥ. የከተማ ሰዎች ሜት ቆርሰው ይሸጣሉ አንደገና ይገዛሉ እርስዎ ይህንን ይደግፋሉ?

መ. በእርግጥ ይህንን እኔም አልደግፈውም የከተማ ሜት ከፍያለ ጥቅም ሊኖረው ይችላል እኔ ግን አልሸጥም ገንዘብ አላቂ ነው፡፡ ሜት ለባለቤቱ እንደሚስት ነው፡፡ ሚስት አትሸጥም

ጥ. በደርግ ጊዜ ሜት እንደምንሰማው ከሆነ በየሁለት ዓመት እየለካ እንደገና ያከፋፍላል አሁን ይሄ ይደረጋል ወይ?

መ. የለም

ጥ. አሁን በኢህአዲግ ዘመን የገበሬ ችግር ምንድን ነው?

መ. በዕድሜዬ በአፄ ኃ/ስላሴ 17 ዓመት አርሻለሁ 17 ጥምድ እያረስኩ ግብርም ከፍያለው በደርግም 17 ዓመት አርሻለሁ በሀይለስላሴ ሜት ለምና ስፋት ነበራት በኋላ ገሙድ ገባ

ጥ. ገሙድ የገባው የተለካው መቼ ነው?

መ. በባለርስት ነው ጋሻ እየተባለ ገሜድ የገባ

ጥ. ቅፅል ስሙ ሽቦ የሚባል ሰው ያውቃሉ ወይ?

መ. ሽቦ ተጣለ ሲባል ታሪክ እናውቃለን ሰወየውን አናውቅም ለአንድ ሰው ነው 5 እና 4 ጋሻ የሚያሳርሰው የሚታረሰው አሁን ሰው በዛ ሁሉም ነገርም ተወደደ ደርግ እንደመጣም መሬት ለአራሹ ተብሎ ተወረሰ ያን ዘመን በቤተሰብ ልክ ነው መሬት የሚከፋፈለው በቤተሰብ ቁጥር ነው 12 ቤተሰብ ያለው ሰው አንድ አንድ ጥማድ የተከፋፈለ ግን አነሰን ስንከፋፈል ደስ ብሎን ነበር ግን ግብርና ኮታ ጫኑብን በዘመኑ አንድ ልጅ ያለውን ግማር ለጦርነት ይልክ ነበር በግዳጅ እሱም ሄደ ይሄ መንግስት ገባ መሬቱም ትልቅም ይሁን ትንሽ እንደያዝን ቀረን፡፡

መሬት አትሸጥም አትለወጥም የመንግስት ናት ስለተባለ የራሴ እስከሆነ ለምን የፈለግነው አናደርግም ለምን ይህንን አስቀማጡብን የራሴን እንደፈለኩ ለምን አላደርግ ኘላን አስነሱ ተብለን አስነስተን ኘላኑም በእጃችን ነው በርግጥ መሬት መሸጥ የለበትም የከተማ ሁኔታ የቆዳ ስፋትም ስላለ ካሳ ተቀብለው ለማዘጋጃ ቢሸጥ ማንም እየከላከለው አይደለም፡፡ አሁን ማዳበሪያ ሲወደድ ከሰው ብዛት ነው ወይንስ ምንድነው እያልን እንጨቃለን ማዳበሪያ በጣም ተወዷል ነጋዴ እጅ ገብቶ ማዳበሪያ በመንግስት እጅ ቢሆን ጥሩ ነው፡፡

ጥ. አሁን አንድ ሀይል መጥቶ የገበሬዎችን ችግራችሁን ልፈታላችሁ እችላለሁ የምፈታላችሁ ግን ከችግሮቻችሁ መሀል አንድ ችግር ብቻ ነው ቢላችሁ የምታስቀድሙት ችግራችሁ ምንን ነው?

መ. ይህንን የጠየቃችሁት ችግራችንን ልትፈቱ ከሆነ መንግስት ገበሬውን ማእከል አድርጌ እሰራለሁ ነው የሚለው ግን ምንም አልተደረገልንም ከህዝቡ 85% ገበሬ ሆኖ ምንም የተደረገለት የለም ዘንድሮ ገበሬው እንዳለ የዘራው በብድር ነው መንግስትም አይቶ ምንም አላደረገም ገበሬው ከመንግስት የማዳበሪያ ወይም የገንዘብ ድጎማ ቢደረግ ለውጥ ይመጣል፡፡

ገበሬው ተለውጧል የሚባለው ካለው ገበሬ ከመቶ ሁለት አይሆንም፡፡ አሁንም ሲሸለሙ የምናያቸው ቀደም ባለው ጊዜ ደህና ቅርስ የነበራቸውም ከብትም የነበራቸው ናቸው እንጂ አሁን የተነሱት አይደሉም፡፡

ጥ. ይሄ ሀሳብ የሁላችሁም ነው?

መ.	አዎ ሃሳቡ የሁላችንም ነው ድጎማ እንዲደረግልን እንፈልጋለን፡፡

እኛም የምናምነው 85% የሚሆነውን ገበሬ ትተን 15% ብቻ ይዘን እናድጋለን ብንል የትም አያደርሰንም ስለዚህ አብረን ሚዲግ አለብን አብረን ካላደግን አብረን ነው የምንወድቀዉ ስህተታችንን አወቀን ከዛ በማሳት ሥርተን ለወጥ ለማምጣት ነው በእርግጥ ለወጥ በቀላሉ አይመጣም፡፡ መንግስት የእህል ዋጋ ላይ ገንዘብ ለሚጨምር ከ10 ዓመት በላይ ነው የፈጀው ስለዚህ ጥናታችንም እነዚህን የመሳሉ ሃሳቦችን በማሰብሰብ ለማሻሻል ነው የምንሠራው

አመሰግናለሁ፡፡